ሚያዝያ 28, 2000

# የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ

## የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪ

ጀግኖች አባቶቻችን ፣ አያቶቻችንና ቅድም አያቶቻችን የጀግንነት ሥራቸውን አሳይተው ቅርስ አሳልፈው የረገፉባትን የአካል እናታችን መጠጊያችን መሸሸጊያችን ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት።

ይህቺ እናት ሀገራችን ዛሬ በጎሣ መሸንሸኗ፣ ባሕር በር አልባ መሆኗ ፣ በራሷ ተራራ ታጥራ ፣ እርሷ ዓለምን ረስታ ዓለምም እርስዋን ረስቷት ልጆቿዋም በዘመናዊ የጎሳ ፈታውራሪዎች ቁም ስቅላቸውን የሚያዩባት ሀገር ሆናለች።

አሁንም ደግሞ እነሆ ቦጥቡጠዋት ያልጠገቡት ፣ ተበቅለዋት ያልረኩት ጎሰኛ ፈታውራሪዎች በንቀት የጦዘው እብሪታቸው ህሊናቸውን ጋርዶት ጀግኖች እናቶቻችንና አባቶቻችን ደም ገብረው አጥንታቸውን ማግረው ያስከበሩትን የሀገሪቱን ድንበር በማፍረስና ተወላጁን ከአጽመ እርስቱ በመንቀል ከጎንደር እስከ ጋምቤላ የሚደርሰውን ግምቱ በቁመት 1600 ኪሎ ሜትር የሚሆነውንና በስፋቱ ከ 30 — 50 ኪ.ሜትር የሚደርሰውን መሬት በላዩና በውስጡ ያቀፈውን ሀብት ከነቅርሳችን ከዚህ በፊት ለሻቢያና ለየመን በሰጡት አኳኋን ዛሬም በንቀትና ማን ምን ያደርገኛል ስሜት ለሱዳን መንግሥት አሳልፈው ሰጥተውታል።

ጉዳዩ የሀገርና የወገን መዘረፍ በመሆኑ በዚሁ አድራጎት ያዘኑ ፣ የተከዙ ፣ አይደረግም ያሉና የተቃወሙ ሁሉ እርሻቸው ተቃጥሏል ፤ ንብረታቸው ተዘርፏል፤ ከቤትና ከኑሮአቸው ተፈናቅለዋል። ያ ብቻ አይደለም ከጣሊያን ወረራ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያዊያን በባእድ ሀገር ሠራዊት ተከበው በቁጥጥር ሥር ውለው ወደ ሱዳን ተግዘዋል። እዚያም ታሥረው በአካላቸውና በመንፈሳቸው እየተሰቃዩ መሆናቸውን ሰምተናል። የድረሱልኝ ጩኸታቸውም እንደቀጠል ነው።

ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ አሳዛኝና አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ በዚሁ ቦታ ላይ በወያኔ / ኢ.ህዴግ እርዳታና ትብብር የሱዳን ጦር በቦታው ላይ ሰፍሮ ይገኛል። ይኸው ወራሪ ጦር ኢትዮጵያዊያን ባካባቢው እንዳይደርሱ ያግዳል ፣ ያሥራል ፣ ይደበድባል ፣ ይገድላል። ይህ በኢትዮጲያ ሕዝብ ላይ የታወጀ ግልፅ ያልሆነ ወረራና ቅሚያ ነው።

ይህ ጉዳይ እጅግ በምሥጢር ሲከናወን ቆይቶ ዛሬ ባደባባይ ይፈፀም እንጂ ወያኔዎች ይህንን የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት የሚመመለከተውን አብይ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በራሱ አምሳል ካቋቋመው ፓርላማም ቢሆን በድብቅ የፈፀመው ጉዳይ ነው።

ይህም ሆኖ ዛሬም እንደ ገና ዳቦ ከፊት የሱዳን ጦር ከኋላ የአጋዚ ጦር የተሰለፈበት ሕዝባችን በስቃይ ላይ ነው። እናም በእነዚህ ከፊትና ከኋላ በተሰለፉ ወራሪዎች መሃከል አጣብቂኝ ውስጥ ገብተው የሚገኙ ወገኖቻችን የድረሱልኝ ጥሪ እያሰሙ ነው።

ይህ ዛሬ በእነርሱ ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥቃት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥቃት ነው። ለዚህ ጥቃት ደግሞ ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ፈጥኖ የሚደርስ ማንም አይኖርምና ቶሎ ፈጥነን በመንቀሳቀስ የሚፈፀምባቸው ጥቃት እንዲቆም ፣ የታሰሩት እንዲፈቱ ፣ የተፈናቀሉት ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ፣ ለወደፊቱም በሀገራቸው የመኖር መብታቸው ተጠብቆላቸው እንዲኖሩና በሕገ ወጥ መንገድ ያለሕዝብ ፈቃድና እውቅና ስልጣንንና ሀይልን መከታ በማድረግ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን ለሱዳን የተሸጠው መሬት እንዲመለስ ኢትዮጵያዊያኑም የመሬታቸው ባለቤት እንዲሆኑ ለማስቻል የጥረታችን መጀመሪያ ያደረግነው ታላቅ ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ በማድረግ ለዎገኖቻችን አለኝታነታችንን ለአገዛዙና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ደግሞ ተቃውሞአችንን ማሰማት ነው።

ይህ የተቃውሞ ሰልፍ የተሳካ እንዲሆን ደግሞ ከጎሰኝነትና ከመንደርተኝነት ስሜት በተላቀቀ ሕሊና በወገኖቻችን ላይ ስለሚፈፀመው ጥቃትና ውርደት ሁላችንም በኢትዮጵያዊነት ስሜት በአንድነት እንድንወጣና ለወገኖቻችን የድረሱልኝ ጥሪ አፋጣኝ መልስ እንድንሰጥ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**የተቃውሞው ሰልፍ ቦታ ኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት**

**ቀን፡- እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሜይ** 19, 2008 (MAY 19, 2008)

**ሰዓት፡- ከጠዋቱ 3 ሰዓት** (9፡00 AM)

የሰልፉ አስተባባሪ ግብረ ሃይል

ለመረጃ በስልክ ቁጥር 202-431-2022 ወይንም 301-270-6658 ይደውሉ